

GBV

# ኢየሱስ

## ብቸኛው እውነተኛ ተስፋችን



ISBN: 978-3-96162-649-6

Published 2020 by GBV
GBV Dillenburg GmbH
Eiershäuser Straße 54
35713 Eschenburg
GERMANY

info@gbv-dillenburg.de
www.gbv-dillenburg.de
www.gbv-online.org

© Stiftung Missionswerk Werner Heukelbach
Original Title: “Jesus unsere einzige Chance”
Text: Manfred Paul

Thanks to pixabay.com for many of the pictures.

# ኢየሱስ

## ብቸኛው እውነተኛ ተስፋችን



የሚያለቅስ ግንብ፣ ኢየሩሳሌም



የጌንሳሬጥ ባሕር

# ኢየሱስ



ስም፡ ኢየሱስ ክርስቶስ

መኖሪያ፡ ናዝሬት

የትውልድ ስፍራ፡ ቤተልሔም

ዕድሜ፡ 30 ዓመት

ሥራ፡ አናፂና ከቦታ ቦታ ተንቀሳቃሽ ሰባኪ

ልዩ መለያው፡ መስህብነት ያለው መልከ መልካም

የተመሰረተበት ክስ፡ ራሱን የእግዚአብሔር ልጅ ማድረግ

ከሳሽ፡ የሃይማኖት መምህራን ኢየሩሳሌም

የፍርድ ውሳኔ፡ የስቅላት ሞት

# ከፍርድ ሂደት መዝገብ ተቀንጭቦ የተወሰደ



የክርስቶስ የእሾክ አክሊል፡ የክርስቶስን የሾክ አክሊል ለማበጀት ጥቅም ላይ የዋለ ነው ተብሎ የሚታሰብ




በቂሳርያ የጲላጦስን ስም የያዘ በድንጋይ ላይ የቀረፀ ጽሑፍ

የይሁዳ ክፍለ ሀገር ገዢ የሚሆን ጲላጦስ ኢየሱስን ሲመረምር "ንጉሥ ነህ?" ሲል ጠየቀው፤

ኢየሱስም መልሶ፤ "እኔ ንጉሥ እንደሆንሁ አንተ ትላለህ፤ እኔ ለእውነት ልመሰክር ስለዚህ ተወልጃለሁ፤ ስለዚህም ወደ ዓለም መጥቻለሁ፤ ከእውነት የሆነ ሁሉ ድምፄ ይሰማል" (ዮሐ.18፡37)



በኢየሩሳሌም ያለ የድንጋይ ወለል (ገበታ)

# ዘመኑና ቦታው፡ ኢየሩሳሌም፤ 33 ዓ. ም.



## ስቅለት

ጲላጦስ ካስገረፈው በኋላ ኢየሱስን በስቅላት ለሚገድሉት አሳልፎ ሰጠው፤ በመቀጠልም ተዘባበቱበት፤ የእሾህንም አክሊል በራሱ ላይ ደፉበት፤ ረጅምና ሹል የሆኑ እሾኮችም ሥጋውን በሳሱት፤ በታላቅ በትርም ራሱ ላይ በርካታ ጊዜ በብርቱ ተመቷል፤ እናም ኢየሱስ በገዛ ደሙ ርሶ ከአሠቃዮቹ ፊት ቆመ፤ በዚህ የመዘባበቻ ሳቅ መካከል የንጉሥነቱ ምልክት የሚሆነውን ቀይ ልብስ አለበሱት፤

በእርግጥ ይህ ሁሉ የሆነ ግልጽ በሆነ አለማመን ነው፤ ከዚያም በፊቱ ተንበርክከው እየሰገዱ በንቀትና በፌዝ “የአየሁድ ንጉሥ ሰላም ላንተ ይሁን” አሉ፡፡



የጥንቷ ኢየሩሳሌም ካርታ


የሮሙ ገዥ የሚቀመጥበት የአንቶኒያ ምሽግ




አውራ ዶሮ በጌቴ ሴማኒ የአትክልት ስፍራ ውስጥ

ወደ ስቅላት እየተወሰደ ሳለ አንድ ሰው የኢየሱስን መስቀል እንዲሸከም ተገደደ፤
በመቀጠልም ስቅላት ተከናወነ፤ እንዲሞት የተፈረደበቱ ኢየሱስ እንደተራቆተ ሥጋው በመሬት ላይ ተጋድሞ ከነበረው የተመሳቀለ እንጨት ጋር በችንካረ ተመታ፤ ቀጥሎም ሥጋው ከምድር በላይ ሦስት ሜትር ከፍ ተደርጎ ከእንጨቱ ጋር ተጣበቀ፤ አንዳንድ ተመልካቾች የተረበሹ መስለው ታይተዋል፤ ከሌሎቹ ፊት ላይ ግልጽ ጥላቻ ይታያል፤ ነገር ግን በድንገት የሌሊት ያህል ጨለማ ሆነ፤ ታላቅ ፅጥታ ምድሪቱን ከደናት፤ ለሦስት ሰዓታት ጨለማ ሆነ፤ ረጅም የጨለማ ሰዓታት፤ ከቀትር በኋላ ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት ያህል ሲሆን ታላቅ ጩኸት ከመስቀል ላይ ተሰማ፤
በመቀጠልም ኢየሱስ ድምፁን ከፍ አድርጎ "ተፈጸመ" ብሎ ጮኸ፤ ሞተም፤ ወዲያውኑ ታላቅ የነጐድጓድ ድምፅ ተሰማ፡፡
ታላቅ የመሬት መናወጥም ምድሪቱን አናወጠ፤ ይህም እንግዳ እጅግ አስፈሪ የሆነ የተፈጥሮ ክስተት ነው፤ ኢየሱስ ሲሞት ያየው የሚገድሉት ሰዎች መሪ የመቶ አለቃ በታላቅ ፍርሃት ተውጦ "በእውነት ይህ ሰው የእግዚአብሔር ልጅ ነበር" አለ፡፡






"በእውነት ይህ ሰው የእግዚአብሔር ልጅ ነበር"



የቀራንዮ ኮረብታ የሚባለው ስፍራ



የመስቀል መንገድ

# በኢየሱስ ሕይወት ዙሪያ ያለው ነገር ገና አላበቃለትም

## ከሦስት ቀናት በኋላም አዲስ ነገር ተከሰተ፤ ሊታሰብ የማይቻልም ነገር ሆነ!

በዘመኑ ኖረው ቢሆን የዜና አውታሮች
እንዲህ ብለው በዘገቡ ነበር፡

ኢየሩሳሌም በድንጋጤ ውስጥ!
የተሰቀለው ኢየሱስ ሕያው ሆነ!
ከሦስት ቀናትም በኋላ በደቀመዛሙርቱ ታየ፤
500 ሰዎች አይተነዋል ሲሉ መሰከሩ፤
ኢየሱስ በእርግጥ ሞቷልን?
በይፋ መሸፋፈን!
ያሳፍራል!
የመቃብር ጠባቂዎች ጉቦ ተቀበሉ!
የዕለት ሁኔታ፡ ዝም በሉ - ታላቅ ምስጢር!

“የምኖርባቸው ቀናት በቁጥር የተወሰኑ ናቸው፡ ነገር ነገር ግን ሕይወቴ የኢየሱስ ነው፤ እናም ኢየሱስ ከሙታን በመነሣቱ ከእርሱ ጋር እኖራለሁ፤ መቃብር የጉዞዬ መደምደሚያ አይደለም።”

# ይህ ኢየሱስ ማን ነበር?



በኢየሩሳሌም ወርቃማው በር በመባል የሚታወቀው ይህ ነው

## ከተማዋ በነውጥ ውስጥ ናት፤ በኢየሩሳሌም ጎዳናዎች ላይ ወሬ ይናፈሳል፡፡

የፍትሕ መጓደል ይሆንን? ለማንኛውም ኢየሱስ ይሞት ዘንድ ለምን ተገባው? ለምን? መሪዎች ለምን በመስቀል ላይ እንዲቸነከር አደረጉት?
አንድ ነገር ግልጥ ነው፤ በመሠረቱ ሕዝቡ ኢየሱስን የሚደግፍ ነበር፡፡
አስቀድሞም እንዲመርጡት ተደርጎ ቢሆን ኖሮ፣ ኢየሱስን ይመርጡ ነበር፤
ሲጀመር እርሱ ይህንን የሮማውያንን ቡድን በስፍራው ለማስቀመጥ የሚበቃ ነገር ነበረው ...

**ነገር ግን ሁሉም ነገር የሆነው ፈጽሞ በተለየ መንገድ ነው፤**

ኢየሱስ ለብዙ ቀናት በከተማው የመነጋገሪያ ርእስ ነበር፤ በግልፀ የኢየሱስ ተከታዮች እንደሆኑ ራሳቸውን ያሳወቁት ይበልጡኑ እየበዙ መጡ ሌሎች ደግሞ እንዳይታወቅባቸው ከተዘጉ ደጃፎች ጀርባ ተደብቀው አሉ፤ ለማናቸውም ሁሉም ኢየሱስ በአካለ ሥጋ እንደታያቸውና ሕያው እንደሆነ ይናገራሉ ይህም በእጅጉ የሚያበሳጭ ንግግር ነው

እያንዳንዱ ሰው ታውኳል፤ በኢየሱስ ዙሪያ ያለውን እንቆቅልሽ ሊፈታ የቻለ አንድም አልነበረም፤ ይህ ሰው በውኑ ማን ነበር? ሕዝብ አሳች ነበርን? ችግር የሚፈጥር? ማኅበረሰብ ለመለወጥ የሚጥር ግብታዊ ነበርን? ወይስ በእርግጥ የእግዚአብሔር ነቢይ?

“ታዲያ ለሌሎች የሰማይ ሕይወት ተስፋ ሰጥቶ ለራሱ እንደ ወንጀለኛ በመስቀል ላይ ካከተመ እርሱ ማን ነው? ወይስ እርሱ በእርግጥ መሢሕ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ሲናገር እንደነበረው እንደዚያው ነው? ያ እውነት ከሆነ አለቀልን!” ይሉ ነበር፡፡

እስከዛሬ ድረስም ጉዳዩ አወዛጋቢ ነው፤ ይህ ኢየሱስን የተመለከተ ጥያቄ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ሊመለስ ይገባዋል፤ ነገር ግን እንዴት? ለአንዳንዶች መልሱ ግልፀ ነው፡፡

አሁንም ቢሆን ኢየሱስ ተአምራት የማድረጉን እውነታ ሊክዱ አይችሉም፤ በእርሱ በኩል ከፍጥረት አቅም በላይ የሆኑ ነገሮች ተከናውነዋል፤ ምልክቶች ተአምራት ሕዝቡን ያስደነቁ ታላላቅ ነገሮች ተደርገዋል፤ እርሱ የረዳቸው ሰዎች ኢየሱስ ከሌሎች የተለየ እንደሆነ አምነዋል፡፡



# በእርግጥ ኢየሱስ ከሙታን ተነሥቷልን?

# ስለ መምህሩ ስለ ኢየሱስ የሚወሩ ወሬዎች

ስለማንነቱ የሚነገሩ እርስ በርሳቸው የሚጋጩ ሐሳቦችን ሰዎች የተናገሩበት እንደ እርሱ ያለ በታሪክ ኖሮ አያውቅም፤ አንዳንዶች በእጅጉ ከልባቸው ያፈቅሩታል፤ ሌሎች ደግሞ ለመግደል በሚያበቃ ጥላቻ ይጠሉታል፤ ብዙዎች ስለ ኢየሱስ ሲነገር ስለሚበሳጩ ስለ እርሱ ከመስማት ራሳቸውን ማራቅን ይመርጣሉ፤ ለምን? ምክንያቱም የእርሱን ነገር እነርሱን የማይመለከት የግል ጉዳይ ያደርጉታል፡፡

## ይሁን እንጂ ይህ ሊስተዋል የሚገባ ነው፡

እርሱ ሁልጊዜም የምስማሩን አናት በትክክል የሚመታ ነው! የሚናገረው ሁሉ ፍጹም እውነትነት አለው፤

ማንም አድርጎት በማያውቀው ልክ ሰዎችን በሚገባ ያውቃቸዋል፤ ከአፉ የሚወጡት ቃላት ሁሉ እውነት ናቸው፤ ወደ እርሱ መጥቶ ትክክል ይሁን የተሳሳተ መሆኑን ሳይገነዘብ የሚቀር የለም፤ እንደ እርሱ የተሰወሩ ሐሳቦችን ወደ ብርሃን የሚያወጣ ሌላ ኖሮ አያውቅም፡፡

ይሁን እንጂ አንድ ሳይነሳ ሊታለፍ የማይችል ነገር አለ፤ ይኸውም ኢየሱስ ብቅ ሲል የሚታወቅ መከራ ሁሉ ከያለበት ብቅ ማለት መጀመሩ ነው፤ ምስኪኑ ሕመምተኛውና በማህበረሰብ ውስጥ የተናቀው ሁሉ ወደ እርሱ ይሳባል፡፡

ኢየሱስ የሚለው ስሙ በተከታዮቹ ጆሮ ላይ ጥዑም ዜማ ነው፤

ብዙዎች ጠላቶቹ ግን ይታወኩበታል፤ ስለኢየሱስ ተነግሮ ስሜት በተነካበት ቦታ ሁሉ ላይ መንፈስ ይለወጣል፤ አመለካከትም ይገለጣል፤

ለምንድነው እንደሞተና ከዚህ ምድር እንደተወገደ ስለሚታሰብ ስለእርሱ ይህን ያህል በስፋት የተጻፈው? ለምንድነው በእርግጥ እንደሞተ የሚጻፈው? ሚሊዮኖች እርሱ ሕያው እንደሆነ እየመሰከሩ ጥቂቶች ሞቷል ብለው ስለሚያስቡት ስለኢየሱስ መጻሕፍትን የሚያሳትሙት ስለምንድነው? መልሶ መላልሶ የኢየሱስ ታሪክ በፊልም የሚቀረጸው ለምንድነው? ወይስ ሰው ሊቀበለው ከሚችለው የሚያልፍ በዚህ ታሪክ ውስጥ ምን አለ? ስለዚህ ስለ ኢየሱስ የወዳጆቹንም ሆነ የጠላቶቹን ትኩረት በእኩል የሚስበው ምንድነው? ኢየሱስ ሆይ አንተ ማን ነህ?



ኢየሩሳሌም ዛሬ



ዓሳ ማጥመጃ ጀልባ በገሊላ ባሕር ላይ

> “ሃይማኖት በአንዳች ነገር ማመን ነው፤ ክርስትና ግን ሕይወትን አጠቃሎ ለኢየሱስ ክርስቶስ መስጠት ነው”

ኢየሱስ መኖሩ በታሪክ ተረጋግጧልን? በ90 ዓመተ ምሕረት ፍላቪየስ ጆሴፈስ የተባለው የአይሁድ ታሪክ ጸሐፊ “ጥንተ ነገር” በተሰኘ ሥራው (18ኛው መጽሐፍ፤ ምዕራፍ 3፤ አንቀጽ 3) ኢየሱስ በታሪክ ስለመኖሩ እንዲህ ሲል ጽፏል፤ “እርሱን ሰው ብሎ መጥራት በሕግ የሚፈቀድ ከሆነ በዚህን ጊዜ ኢየሱስ የተባለ ጥበበኛ ሰው ነበረ፣ ድንቅ ሥራዎችን የሚሰራ ነበረ፣ እውነትን በደስታ የሚቀበሉ ሰዎች አስተማሪ ነበር፤ ከአይሁድም የሆኑ ከአሕዛብም የሆኑ ብዙዎች ወደ እርሱ ይመጡ ነበር፡ እርሱ ክርስቶስ ነበር፤ በመካከላችን ዋነኞቸ ሰዎች እንደመሩት ጲላጦስ እንዲሰቀል ባደረገው ጊዜ ከመጀመሪያው ይወዱት የነበሩት እርሱን አልተውትም፣ በሦስተኛው ሕያው ሆኖ እንደገና እንደሚታያቸውና እርሱን የሚመለከቱ ሉሎችን አሥር ሺህ ድንቅ ነገሮችን የመለኮት ነቢያት አስቀድሞ በተነበዩለት መሠረት ታይቷቸዋልና፡፡”

# ኢየሱስ መኖሩ በታሪክ ተረጋግጧልን?



"ተገቢ የሆነ ብቸኛው ድምዳሜ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ነው"



አምስት ዳቦዎችና ሁለት ዓሳዎች

ከመጽሐፍ ቅዱስ በተጨማሪ ስለ ኢየሱስ ሕይወት የሚመሰክሩ ሌሎች መረጃዎች አሉ፡፡ ለምሳሌ ሮማዊው ባለታሪክ ታሲተስ፣ በአጼ ሐድሪያን ሥር የሮም ቤተመንግስት ሹም የነበረዉ ስዩቶኒየስ እና በታናሿ እስያ የቢታንያ ሮማዊ ገዢ የነበረው ታናሹ ፕሊኒ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

በጦርነቱ እስከ አውሮፓ እኩሌታ ድረስ ፍርሃትን ያስፋፋው ናፖሊዮን በሕይወት ዘመኑ ፍጻሜ ላይ የሚከተለውን ጽፏል፤ "በዚህ ሁሉ የጦር ጀኔራሎቼ በሩብ ምዕተ ዓመት ሙሉ አንድ አህጉር ስንኳ መማረክ አልቻልኩም፣ ይህ ኢየሱስ ግን የጦር መሣሪያ ሳይታጠቅ ሕዝብንና ባህሎችን ሁሉ በአንድ ሺህ ዓመት ማረከ፡፡"

# እውን



"በሰማይ እግዚአብሔር የየትኛው
ቤተክርስቲያን አባል እንደሆንኩ
ከቶውንም አይጠይቀኝም፣
ብቸኛውና የሚገደው ነገር
የኃጢአቴን ስርየት በኢየሱስ
ክርስቶስ ተቀብዬ እንደሆነና
እንዳልሆነ ነው"

# ኢየሱስ የዓለምን ታሪክ ሊሠራ ፈልጓልን?



ኢየሱስ በሥጋ ተገልጦ በነበረበት ዘመን የነበረው የሄሮድስ ቤተመቅደስ ተምሳሌት

ፈጽሞ አይደለም፣ ራሱ “መንግሥቴ ከዚህ ዓለም አይደለችም” ብሏልና (ዮሐ. 18፡36)

ኢየሱስ የዚህን ዓለም ታሪክ ለመሥራት ፈልጎ ቢሆን ኖሮ እንደ ጦር ጄኔራል ይህን ዓለም ወደ መግረክ በሄደ ነበር፣ ያም ቢሆን የሚከናወነው በቤተመንግሥት በተወለደ ንጉሥ እንጂ ልብን ከሁለት የሚተረትር የሚያሳዝን ታሪክ ባለው ሕጻን ነውን? በዚያ በሚያሳዝን የእንስሳት ግርግርም ከበሬ እና ከአህያ ጋር በተኛ? ሰዋራ በሆነች በቤተልሔም ከተማ በተወለደ? በጥያቄ ላይ ጥያቄ ማንሳት ይቻላል፤

ይሁን እንጂ ኢየሱስ በዚህ ዓለም ታሪክ ላይ ያመጣው ለውጥ የሚካድ አይደለም፤ በመለኮታዊ ትምህርቱና የእግዚአብሔርን ፍቅር እና ምሕረት በሚመለከት ይዞት በመጣው ሥር ነቀል ዜና ፈውስን፣ የነፍስ መዳንንና ዘላለማዊ ሕይወትን ቁጥር ስፍር ለሌላቸው ሕዝቦች አምጥቷል፤ ይህም ያን ጊዜ በእስራኤል ላይ በኋለኞቹ ቀናትም በዓለም ሁሉ ላይ እስከ ዛሬ ድረስም እየሆነ ይገኛል፡፡

የእግዚአብሔር በእስራኤል በኩል መገለጥ፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ማንነትና መጽሐፍ ቅዱስ ላይለያዩ ተጋጥመዋል፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ላልዳነውና እየሞተ ላለው ዓለም ያቀረበው ስጦታ ነው፤ ይህን ለመገንዘብ በእግዚአብሔር የበሩ ዓይኖች ያስፈልጋሉ፤ በእግዚአብሔርና በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ የሚዘብቱና የእግዚአብሔርን መኖር የሚክዱ ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስ ስለእነርሱ የሚናገረውን ማወቅ ይኖርባቸዋል፤ በልባቸው “አምላክ የለም” የሚሉት የሚኖሩት ከእውነታው ውጭ ነው (መዝ 13(14)፡1)፣

“... ይህን ከጥበበኞችና ከአስተዋዮች ሰውረህ ለሕጻናት ስለገለጥህላቸው አመሰግንሃለሁ” (ማቴ 11፡25)፡፡

“በሰማይ እግዚአብሔር የየትኛው ቤተክርስቲያን አባል እንደሆንኩ ከቶውንም አይጠይቀኝም፣ ብቸኛውና የሚገደው ነገር የኃጢአቴን ስርየት በኢየሱስ ክርስቶስ ተቀብዬ እንደሆንና እንዳልሆነ ነው”




ጀኔራል ሌው ዋላስ “አምላክ የለም” በሚለው ክህደቱ በሚገባ የታወቀውን ኮሎኔል ኢንገርሶልን በባቡር ጉዞ ላይ እንዳለ አገኘው፣ “ክርስትና ትርጉም የለሽ ነው” ስለሚለው ሐሳብና ስለሌላም ከፀሐይ በታች ስላለው ብዙ ነገር ተወያዩ፡ ኢንገርሶልም ዋላስን እንዲህ ሲል አነሳሳው፣“ ብልህና የተማርክ ሰው ነህ፣ ክርስትና በእርግጥ ትርጉም የለሽ መሆኑንና ኢየሱስ ክርስቶስ ፈጽሞ እንዳልኖረ አስረግጦ የሚናገር መጽሐፍ ለምን አትጽፍም! ያም መጽሐፍ ያለጥርጥር ከልክ በላይ ከሚሸጡት መጻሕፍት አንዱ ይሆናል” አለው።

ዋላስም በታላቅ ስሜት ሥራውን ተያያዘው፤ ዝነኛ ሊሆን እንደሚችል እያሰበ ይመስጥ ነበር፣ ለመጽሐፉ የሚሆነውን ነገር በመሰብሰብ ዓመታትን አሳለፈ፤
ሆኖም በሙብረቅ እንደተመታ ያህል ኢየሱስ ክርስቶስ በእርግጥ ስለመኖሩ በተገነዘበበት ሰዓት የመጽሐፉን አራት ምዕራፎች ጽፎ ነበር፤
ከዚያም በላይ ኢየሱስ ታሪክ የሚተርክለት ከመሆን ያለፈ እንደሆነም አመነ፤ በሃምሳ ዓመቱ በሕይወቱ ለመጀመሪያ ጊዜ ዋላስ በጉልበቱ ተንበርክኮ ጸለየ፤ የእግዚአብሔርን ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስን

# ቤን ሁር፣ እጅግ ሲበዛ የተዋጣለት

## በዓለም ላይ የሚሊዮኖችን ትኩረት የሳበ ፊልም



ሌው ዋላስ

እንዲያድነው በመጠየቅ ሙሉ ሕይወቱን ለእርሱ አሳልፎ ሰጠ፤

በመቀጠልም የመጽሐፉን አራት ምዕራፎች መልሶ ለመጻፍ ወሰነ፤ መጽሐፉም ሲበዛ የተዋጣለትና ከልክ በላይ የተሸጠ ሆኖ በኋላም የፊልም ቤት የትኬት መሸጫዎችን በዓለም ሁሉ በተመልካች ያጨናነቀውን ቤን ሁር የተሰኘውን ፊልም ያስገኘ ሆነለት፤ ጄኔራል ዋላስም በዚህ አይነት ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ እምነት ፈጽሞ የተለወጠ ሰው አስደናቂ ምሳሌ ሆነ፡፡

የእግዚአብሔር ምስጢራት በሰው ዓይኖች ተለይተው ሊታወቁ አይችሉም፣ ራሱ እግዚአብሔር በሚከፍታቸው የልብ ዓይኖች የሚታዩ ናቸው እንጂ በምክንያት ላይ በሚደገፈው የሰው አስተሳሰብ ሥርዓትም ሊታወቁ አይቻሉም (ኤፌ. 1፡18ን ያንብቡ)፡፡

“ልበ ንጹሖች ብፁዓን ናቸው፣ እግዚአብሔርን ያዩታልና”(ማቴ5፡8)

“... ይህን ከጥበበኞችና ከአስተዋዮች ሰውረህ ለሕፃናት ስለ ገለጥህላቸው አመሰግንሃለሁ” (ማቴ. 11:25)

# … እና አሁንም እየጻፉ ናቸው…!

አንዳንድ የዜና መጽሔቶች ያለማቋረጥ ቤተክርስቲያንን፣ ክርስትናንና በኢየሱስ ማመንን ይቃወመሉ፤ የክርስትና የሆነውን ሁሉ «ማሰብ የጎደለው» አድርገው ይፈርጁታል፤ ሳይንሳዊ መረጃ የሌለው ሐሳብ ብለው ያቃልሉታል፣ ጊዜ እንዳለፈበት ይቆጥሩለታል፤

ነገር ግን እውነትን ፊት ለፊት በመጋፈጥ ፈንታ ምናባዊና ያልተጨበጡ ሐሳቦችን ይዘው ይከራከራሉ፤ እውነትንም ሳያዩት ይቀራሉ፤ እንዲህ ባለው እውቀትን በተሞላ ማጭበርበር ሰው ራሱን ቢያታልል ከራሱ ሌላ ማንን ያጎድላል?

ነገር ግን አንድ ነገር እርግጥ ነው፡
“አንድ ሐሳብ ውድቅ ሊሆን የሚገባው ያን ሐሳብ ሊሽር የሚችል ተቃራኒ መረጃ ሲቀርብ ብቻ ነው፡፡”

መጽሐፍ ቅዱስ የተሳሳተ ስለመሆኑ የሚናገር መረጃ ቀርቦ አያውቅም፤ እያንዳንዱ ሐሰተኛነትና ውሸት በመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ፊት ይፈርሳል፣ ይበታተንማል፡ ስለሆነም የኢየሱስ ተቃዋሚዎች ቃሉን ማጥቃት በከንቱ ይቀጥላሉ፣ ኢየሱስም “ሰማይና ምድር ያልፉሉ ቃሌ ግን አያልፍም” አለ (ማቴ 24፡35)፡፡

“እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወትን ሙሉ በሙሉ ሊለውጥ የሚችል ሌላ ማንም የለም”



# ... አስፈሪ ነው!

በመሠረቱ በክርስትና ውስጥ ያሉ የክርስትና ግንባር ቀደም ጠበቆች እምነታቸውን እንደሚገባ ሊወክሉ ባለመቻላቸው ጥፋተኞች ናቸው፤ የኢየሱስ የምስራች በሆነው ወንጌል ላይ እየተሰራ ያለውን ማየቱ አስፈሪ ነው፣ በእግዚአብሔር ስም ከተሠሩት በርካታ የተናቁ ነገሮች ውስጥ በመካከለኛው ዘመን በመስቀል ጦረኞች/ክሩሴድ/ የተከናወነው አሳፋሪ ድርጊትና በኋላም ከሞላ ጎደል ንጹሐን የሆኑ ሰዎች የተለየ እምነት ይዘዋል ተብለው "በመናፍቅነት" ስም በቤተክርስቲያን እየተከሰሱ በሚዘገንን መልኩ ይገደሉ የነበሩበትን ሁኔታ መጥቀሱ በቂ ነው፤ በእርግጥ ክርስትና ያልሆነ በክርስትና ስም የሚስፋፋ ብዙ አለ፤ ክርስትና ሳይሆን "ነኝ" ብሎ ራሱን በሚጠራው ውስጥ ሁሉ ክርስቶስ የለም፡፡

"ክርስቲያን በሆንኩ ጊዜ እልፍ የሆነ ሸክም ያህል ከነፍሴ ላይ ተንከባሎ ወደቀ፣ አስፈሪው የበደለኝነት ሸክም ከላዬ ላይ ሄደ፤ አሁን በሕይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ ሊከለከል የማይችል ሳቅ ምን እንደሆነ አወቅሁ"



# የሚደንቅ አይደለም...

የመላውን መጽሐፍ ቅዱስ የበላይነት በድፍረት የሚቀበሉ ሰዎች ቁጥር እንደዚህ ጥቂት የሆነው ስለምንድን ነው? ተራው ወንድ ወይም ሴት ተስፋ ቆርጦ ከቤተክርስቲያን ቢመለስ ለምን ይደንቃል?

ብዙዎች ሰዎች የሚሰብኩት ምውት ከሆነ መድረክ መሆኑ የሚያስደንቅ ነውን? ይሁን እንጂ የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነው! ታዲያ የእግዚአብሔር ቃል ለሕይወትና ለእምነት መሠረት ሆኖ የሚያገለግልበት ስፍራ የት ነው? ኢየሱስ ክርስቶስና የእግዚአብሔር ቃል በግልጥነት በሚሰበኩበት ቦታዎች ሕዝብ ለእምነት የሚሆነውን ያገኛል፡

በባህላዊ ክርስትናና በቅዱሳት መጻሕፍት በኩል እግዚአብሔር እኛን በሚጠይቅበት ጥያቄ መካከል ልዩነት መኖሩን መገንዘብ ይኖርብናል፤ አብያተክርስቲያናት ወይም የክርስቲያን ቡድኖች የቅዱሳት መጻሕፍትን መሠረት ለቀው ሲሄዱ ያላቸውን ተሰሚነት ወይም ስልጣን ያጣሉ፤ በግራ መጋባት ውስጥም ይወድቃሉ፤ ታማኝነታቸውን አጥተው መሳለቂያ ይሆናሉ፤ ሰው በዚህ ዘመን መንፈስና አምልኮት የተላበሱ ልበወለድ ትምህርቶችና ረቂቅ አሰራሮች ለሚያስከትሉት ምትሃት ልቡን ከፍቶ ከሰጠ እውር እውርን ወደሚመራበት ሁኔታ ወዲያውኑ የሚገባ አይደለምን? ቤተክርስቲያንም ለዓለም የምትመሰክር በመሆን ፋንታ “የዓለም ቤተክርስቲያን” ትሆናለች፡፡

መሄጃ አቅጣጫ ለጠፋበት ዓለም በሚገባ የሚያበራ መብራት በመሆን ፈንታም የሚያስት መብራት ትሆናለች፡፡



የሚያስቱ ደብዛዛ መብራቶች



“የሕጻናት ጥምቀት ክርስቲያኖች
የሚያደርገን እንደሆነ አስብ
ነበር፤ ይህ ደግሞ አደገኛ
ስህተት ነው፤ መጽሐፍ ቅዱስ
ሰው በንሰሐ፣ በእምነትና
የግል ሕይወቱን ለኢየሱስ
ክርስቶስ በመስጠት ክርስቲያን
እንደሚሆን በግልጥ ይናገራል”

ሀብል አጉሊ መነጽር






የመጽሐፍ ቅዱስ፣ ዋነኛ ሐሳቡ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፣ መርከበኞችን ለመምራት እንደተሠራና ብርቱ መብራት እንዳለው የመብራት ማማ ብርሃኑ ደምቆ የዓለም ታሪክ ማዕበል ውስጥ ያበራል፤ ለብዙዎች እንደጠፉች የበረሃ ገነት ነው፤ እናም መጽሐፍ ቅዱስን ወደጎን መተው መንፈሳዊ ግዴየለሽነትንና የበዛ ግራ መጋባትን ማስከተሉ የሚደንቅ አይሆንም!

ኢየሱስ ክርስቶስና መጽሐፍ ቅዱስ ባለመለያየት አንድ ላይ ተጣምረዋል፤ ሰው መጽሐፍ ቅዱስን ሲያነብ ዘላለማዊነት ያለው እስትንፋስ ያልፍበታል፡፡

በእግዚአብሔር ድምፅም ይማረካሉ፣ ሉዓላዊነቱ በእጅጉ የሚመስጥ በመሆኑ የሚያነበው ሁሉ ለመጽሐፍ ቅዱስ ብርቱ ሐሳብ እጁን ይሰጣል ወይም ይሸሸዋል፡

# መጽሐፍ ቅዱስ ከሁሉ የላቀ መጽሐፍ!

## በዓይነቱ ልዩ የሆነ!



## ስለመጽሐፍ ቅዱስ ማወቅ ያለባችሁ ነገሮች እነዚህ ናቸው

ተጽፎ ለማለቅ ከ1600 ዓመታት በላይ ጊዜ ፈጅቷል (1500 ከክ.በፊት እስከ 100 ዓ.ም)

አርባ የሚያህሉ ጸሐፊዎች ጽፈውታል፡ ከነዚህም ነገሥታት፣ እረኛ፣ አሳ አጥማጆች፣ ካህናት የመንግሥት ባለስልጣናት ወዘተ ይገኙበታል፡፡

ብዛቱ፡ 66 መጻሕፍት፣ ከ1000 በላይ ገጾች!

ርእሰ ጉዳይ፣ እግዚአብሔር ለሰው ያለው የማዳን እቅድ

ትኩረት፡ ኢየሱስ ክርስቶስ

መለያው፡ የእግዚአብሔር እስትንፋስ መሆኑ

በእግዚአብሔር መንፈስ በተነዱ ቅዱሳት ነቢያት በእግዚአብሔር ትእዛዝ የተጻፈ በሰማያዊ ኃይል የተጠበቀ፣ ግድፈት የሌለው ትክክል፣ በሺህ በሚቆጠሩ ቋንቋዎች የተተረጎመ፣ እስከ አሁን ድረስ ባለመለወጥ የተጠበቀ፣ ሚሊዮኖች የሚያነቡትና የሚያፈቅሩት፡፡

በጥልቀት ለመረዳት፡ “መጻሐፍ ቅዱስ እንዴት እንደተገኘ” የሚለውን የዊሌም ጄ ጄ ግላሾወርን መጽሐፍ ማንበብ የሚመከር ነው፡

> “የሕይወት ገጠመኞቼን ለመታገሥ የቻልኩት ኢየሱስ እንደሚወደኝ፣ ማንነቴ እንደሚገባውና እንደሚያጽናናኝ ስለማውቅ ነው”

## በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔርን ለመግለጥ ያገለገሉ ስሞች፣ ማዕረጋትና ባሕርያት በአዲስ ኪዳን ኢየሱስን ለመግለጥ አገልግለዋል፤ ይህም ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ እንደሆነ ቀጥተኛ አመልካች ነው፡፡

"እርሱ እውነተኛ አምላክና የዘላለም ሕይወት ነው"
1ዮሐ.5፡20

ቀጥሎ ያሉት ከብሉይ ኪዳን የተመረጡ ውስን ጥቅሶች ናቸው፤ በትንቢትነት የእግዚአብሔር ልጅ የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን ያመለከታሉ፤

ፍጻሜያቸውም በአዲስ ኪዳን ይገኛል፡

### ስለ ኢየሱስ መምጣት .

ልደቱ፡ ኢሳ9፡5-6፣ 7፡14
ፍጻሜ፡ ሉቃ1፡26-38፣ 2፡1-20

ስለሚወለድበት ስፍራ፡ ሚክ5፡2
ፍጻሜ፡ ሊቃ2፡4፣15

ወደ ግብጽ መሰደዱ፡ ሆሴ11፡1
ፍጻሜ፤ ማቴ2፡14-15

ስለ ተልእኮው፡ ኢሳ59፡20
ፍጻሜ፡ ማር10፡45፣ ሮሜ3፡24

ስለተአምራቶቹ፡ ኢሳ35፡5-6፣ 42፡7
ፍጻሜ፡ ማቴ11፡5፣ ሉቃ18፡35-43፣ ወዘተ

መከራ እንደሚቀበልና እንደሚጠላ፡ መዝ55(56) ና መዝ.68(69)
ፍጻሜ፡ ማቴ.26፡3-4፤ ሉቃ.19፡14

ለ30 ብሮች በይሁዳ ተላልፎ እንደሚሰጥ፣ ዘካ.11፡12፤ መዝ.54(55)፡12-14፣20-21
ፍጻሜ፡ ሉቃ.22፡1-6፤ ማቴ.26፡47-54፤ ማቴ.27.3-10

በሐሰት እንደሚከሰስ፡ መዝ.108(109)፡1-4፤
ፍጻሜ፡ማቴ.26፡59-60

እንደሚዘበትበት፡ መዝ.21(22)፡6-7
ፍጻሜ፡ ማቴ.27፡27-30፤ ሉቃ.23፡35-37፡፡

ስቅለቱ፡ መዝ.21(22)፡14-17
ፍጻሜ፡ ማቴ.27፡32-56፤ ዮሐ.19፡17-18

ለጠላቶቹ እንደሚጸልይ፡ መዝ.108(109)፡4
ፍጻሜ፡ ሉቃ.23፡34






# መጽሐፍ ቅዱስ ስለኢየሱስ ምን ይላል?

## አስገራሚ ግኝት!

ይቅርታ

ማቴ.26፡28፤
ቆላ.1፡14፤ 2፡13
ዕብ.9፡22፤ 10፡18
ኤፌ.1፡7

በደም መግዛት (መዋጀት)

1ቆሮ.6፡20
ራእ.5፡9

እውነተኛ ሰው

በምድር ላይ

ሮሜ 8:3፤
1ጢሞ. 3:16

መጽደቅ

የሐ.ሥ. 13፡39
ሮሜ3፡24፤ 4፡25፤ 5፡29
1ቆሮ.6፡11

መንጻት

1ዮሐ.1፡9
ዕብ.9፡14፤ 9፡22

በመስቀል ላይ እንደሚጮህ፡ መዝ. 21(22)፡1-2
**ፍጻሜ፡** ዮሐ.19፡30

በወንበዴዎች መካከል እንደሚሰቀል፡ ኢሳ.53፡9፤ 12
**ፍጻሜ፡** ሉቃ.23፡33

ልብሱ በዕጣ እንደሚከፋፈል፡ መዝ.21(22)፡18
**ፍጻሜ፡** ዮሐ.19፡24

አጥንቱ እንደማይሰበር፡ መዝ.33(34)፡20
**ፍጻሜ፡** ዮሐ.19፡33፤36

እንደሚወጋ፡ መዝ.21(22)፡16፤ ዘካ.12፡10
**ፍጻሜ፡** ዮሐ.19፡18፤34

በፈቃደኝነት እንደሚሞት፡ መዝ.39(40)፡6-8
**ፍጻሜ፡** ዮሐ.19፡24

ስለሌሎች በምትክነት መከራ እንደሚቀበል፡ ኢሳ.53፡4-6፤12
**ፍጻሜ፡** ማቴ.8፡16-17፤ 1ጴጥ.2፡24

ስለ ትንሣኤው፡ መዝ.15(16)፡9-11፤ 29(30)፡3፤ 117(118)፡17
**ፍጻሜ፡** ዮሐ.20

ወደ ሰማይ እንደሚያርግ፡ መዝ.67(68)፡18፤ 109(110)፡1
**ፍጻሜ፡** የሐ.ሥ.1፡9-11፤

ዳግመኛ እንደሚመጣ፡ ዘካ12፡10፤14-፡3-5፤
**ወደፊት እንደሚፈጸም፡** 1ተሰ.4፡13-18፤ ራእ.19 እና 20፡፡

## ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ነው!

በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ንባቦች ይህን ድንቅ እውነት ይገልጣሉ፤ ለምሳሌ እነዚህን ያንብቡ፡

ዮሐ.1፡11

1ዮሐ.5፡20

ሮሜ 9፡5

ዕብ.1፡8-10

ቲቶ 2፡13

ዮሐ.10፡30

ዮሐ.14፡9

ሕይወቱ፡ ኢሳ.53፡1-3

ጠባዩ፡ ኢሳ.42፡1-2፤6-7፤ 61፡1

መጠላቱ፡ ኢሳ.49፡5-7፤ 53፡1-2

አሟሟቱ፡ መዝ.21(22)፡6-7፤ ኢሳ.53፡8፤ ዳን.9፡26

የሞተለት ዓላማ፡ መዝ.21(22)፤ ኢሳ.53፡6፤ ዳን.9፡24

ትንሣኤው፡ መዝ.15(16)፡9-11፤ የሐ.ሥ.2፡24-28

ወደ ሰማይ ማረጉ፡ መዝ.67(68)፡18፤ ኤፌ.4፡8

ዳግመኛ መምጣቱ፡ ዘካ.14፡4

የተነገሩ ትንቢቶችና ኪዳን ፍጻሜያቸው

“ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና እስከ ዘላለም ያው ነው” (ዕብ.13፡8)

ሦስትነት ያለው አምላክ

“የነበረው ...” ራእ.1፡4

**A**
አልፋ ራእ.22፡13

**ክርስቶስ ከዘላለም በፊት የነበረ**

## ቃል
ዮሐ.1፡1-3

## ኤልሻዳይ (= ሁሉን ቻይ አምላክ)
ዘፍ.17፡1



| ዘላለም ሥነፍጥረት | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | የዓለምና የሰው መፈጠር ዘፍ.1<br>ሰው ወደ ኃጢአት ወደቀ ዘፍ 3 | ከኤድን ገነት መባረር<br>የጥፋት ውኃ፣ የኖኅ መርከብ ዘፍ.6-9 | የባቢሎን ግንብ ዘፍ 11 | እስራኤል በግብፅ ዘጸ.1-11 |
| የሚገኝበት ዘመን ይህ ነው፡ | የኤድን ገነት ዘመን ዘፍ.1-3 | የሥነ ልቡና ዘመን ዘፍ.4-9 | ሰው አገዛዝ ዘመን ዘፍ.10-11 | የአባቶች ዘመን (አብርሃም፣ ይስሐቅና ያዕቆብ) ዘፍ.12-50 |
| መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡ | “ዓለሞች በእግዚአብሔር ቃል እንደ ተዘጋጁ፥ ስለዚህም የሚታየው ነገር ከሚታዩት እንዳልሆነ በእምነት እናስተውላለን።” ዕብ.11:3 | “እግዚአብሔርም የሰው ክፋት በምድር ላይ እንደ በዛ፥ የልቡ አሳብ ምኞትም ሁልጊዜ ፈጽሞ ክፉ እንደ ሆነ አየ።” ዘፍ.6:5 | | |

የኢየሱስ አገልግሎት — **ነቢይ**

# የክርስቶስ ሕይወትና ሥራ

## ዘመናት ሳይቆጠሩ በፊት፣ ለዘመናትና ለዘላለም ያለው ክብሩ (ዮሐ.17፡1፤5)




"ሕግን ሁሉ የሚጠብቅ፥ ነገር ግን በአንዱ የሚሰናከል ማንም ቢኖር በሁሉ በደለኛ ይሆናል፤"
ያዕ.2:10

"ለኃጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር፥ እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ፤"
1ጴጥ.2:24

"በነገው ዮሐንስ ኢየሱስን ወደ እርሱ ሲመጣ አይቶ እንዲህ አለ። እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ።"
ዮሐ.1:29

## ካህን




መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡ "በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ አሉት"
ሐዋ.16:31

"በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው።"
1ዮሐ.1:9

"ከዚያም በኋላ እኛ ሕያዋን ሆነን የምንቀረው፥ ጌታን በአየር ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን፤ እንዲሁም ሁልጊዜ ከጌታ ጋር እንሆናለን።"
1ተሰ.4:17

# የክርስቶስ ሕይወትና ሥራ



# የኢየሱስ ተደናቂነት

## እንደ ኢየሱስ ዓለምን የለወጠ ሌላ ኖሮ አያውቅም



የገሊላ ባሕር ባሻገር ሲታይ

ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ቃል በታላቅ ሥልጣን ይሰብክ ነበር፤

90% የሚሆነው በየዓይነቱ ልዩ ልዩ የሆነው ሕጋችንና ባሕላችን የተገኘው ከመጽሐፍ ቅዱስ ነው፤

ስለጋብቻና ስለ ቤተሰብ ስለ ሰው ልጅ ሕይወት ክቡርነትና ስለ አካባቢ ጥበቃ ይናገራል፤ ስለማኅበራዊ መዋቅራችንና ለችግረኛው ሊደረግ ስለሚገባው እንክብካቤ ይናገራል፡፡ ስለዜግነት ሥርዓትና ለሕይወት ስለሚደረግ ጥበቃ ይናገራል፡፡

ኢየሱስ ሙሉ በሙሉ ራሱን የገለጠው መጽሐፍ ቅዱስ ከሚናገረው ነገር ጋር ነው፡፤ እርሱ ራሱ ሰው የሆነ የእግዚአብሔር ቃል ነው፡፡ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያለውን ሊለካ የማይችል ፍቅር ልናውቅ የምንችለው በእርሱ በኩል ብቻ ነው

ኢየሱስ ወደ እኛ የመጣው ለዚሁ ነው፤ እንደ እኛ ሰው የሆነው ለዚሁ ነው፤ በእርግጥ ሰዎች ቀርበው ይዳስሱት የነበረ ቢሆንም እርሱ ግን ኃጢአት የሌለው ነበር፡፡ እርሱ "ሊዳሰስ የሚችል" በሁለት እግሮች የሚራመድ የእግዚአብሔር ቃል ነበር፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እርሱ እንዲህ ይላል፡

"ቃልም ሥጋ ሆነ .... በእኛ አደረ ... .. ክብሩንም አየን" (ዮሐ.1፡14)

እግዚአብሔር በኢየሱስ ለሰውም ሆነ ለእርሱ መለኮታዊ ማንነት በሚበቃ ልክ ተናገረን፡፡

ዕብራውያን 1፡1-2 እንዲህ ይላል፡- "ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ፥ ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን" ንግግሩም ግልጥና ሊገነዘቡት የሚቻል ነው፡፡

# ኢየሱስ ሕያው ሆኖ ይኖራል - በእርግጥም ሕያው ሆኖ አለ



በሳይንሳዊ ምርምር ፍላጎት ያለው ሁሉ ይህን ያውቃል፤ አንድን የምርምር ሐሳብ እውነተኛ ለማድረግ የሚጠቀሱ ዘዴዎችን በማናቸውም ጊዜ አስቀድሞ የተገኙትን ውጤቶች ማግኘት ይኖርባቸዋል፤ ለምሳሌ ያህል ሁለት ፖዘቲቭና ኔጋቲቭ የሆኑ የተጣሉ ሁለት የኤሌክትሪክ ማስተላለፊያ ገመዶች እንዲነካኩ ቢደረጉ እሳት ይፈጥራሉ፤ ይህ ቦታና ጊዜ ሳይለይ በሁኔታዎች ሳይወሰን ይሆናል፤ ውጤቱም ሁል ጊዜ አንድ ነውና ኤሌክትሪክ ኃይል እውን ይሆናል፤ ስለሆነም በአለማወቅ ምክንያት የኤሌክትሪክን ህልውናን መካድ ሞኝነት ይሆናል፡፡

ኢየሱስንም በተመለከተ ያለው ይኸው ነው፤ የኢየሱስ ህልውና በግል ሊያውቁት የሚቻል የመሆኑ ሐሳብ በማናቸውም ጊዜ ሊረጋገጥ ይችላል፤ በየትውልዱ ሁሉ በኢየሱስ ያመኑ ሕዝቦች ኢየሱስ አዳኝ፣ ፈዋሽ፣ ጠባቂና ታዳጊ እንደሆነ መልሰው መላልሰው ተለማምደዋል፤ ኢየሱስ ከከፋ ውድቀት ነጻ አውጥቶ ፈጽሞ አዲስ ሕዝብ እንደሚያደርግ አይተዋል፤ በኃጢአተኝነት ላይ ድልን ተቀዳጅተዋል፤ በጨለማ ኃይላት ላይ ሁሉ ድልን ተቀዳጅተዋል፡፡

ኢየሱስ እውነት ነው! ኢየሱስ ሕያው ነው!

ያኔ እንደነበረ አሁንም ነው፤ በግል ልትተዋወቁት ትችላላችሁ፡፡

> “የሚያሳዝነኝ አንድ ነገር ቢኖር - ሕይወቴን ለኢየሱስ ቀደም ብዬ አለመስጠቴ ነው”

# ማይክ ታሪኩን ይናገራል



“አሥራ ሦስት ዓመት ሲሆነኝ ከወሮበሎች አንዱ ነበርኩ፤ ሀሺሽ ቢራና ሌሎች ጠንካራ ነገሮች የምፈልገውን ግለት ይሰጡኝ ነበር፤ ብዙ ጊዜ ችግር ውስጥ እገባ ነበር፤ ግጭትና ጠብም የተለመዱ ናቸው፤

ነገሮች ሁልጊዜም ተመሳሳይ ቅደም ተከተል ነበራቸው፤ መያዝ፣ ለፍርድ መቅረብ፣ ጥፋተኛ ሆኖ መገኘትና የእስራት ፍርድ መቀበል ወይም ብዙውን ጊዜ የገንዘብ መቀጮ መቀበል ነው፡፡ ነገር ግን ሊረዳኝ የቻለ አልነበረም፤ ከእስራት እንደተፈታሁ ወዲያውኑ ወደቀደመው መንገድ እመለሳለሁ፤ እኔ ባለሁበት ሳይዘረፍ የሚቀር መደብር የለም፤ ባለማቋረጥ እሰርቅ ነበር፤ በጣም አስፈሪ ነበር፡፡ ከዚያም አስደንጋጭ ነገር ሆነ፤ በስልክ እንጨት ተሸሽገን ከመካከላችን አንዱ ሞተ፤ ታላቅ ድንጋጤ ወደቀብኝ፡፡ ከሆስፒታል ከወጣሁ በኋላ ሥራ ፍለጋ ቀጠልኩ፤ እዚያና እዚያ የተገኘውን ሥራ ሠራሁ፤ ከዚያም የተሻለ ሐሳብ መጣልን፤ ሙዚቀኞች እንሆናለን፣ ባንድ እናቋቁም አልን፤ በምንጫወትባቸው የመዝናኛ ስፍራዎች ላይ ያለው የበዛ ጠጪነት እኔን የአልኮል ጥገኛ አደረገኝ፤ በእነዚህ ወጥመዶች ተያዝኩ፤ የምስጢር ወዳጄ አልኮል ሆነ፤ በዚያ ላይም ሃሺሽ ይጨመርበታል፤ የገዛ ስሜን መጻፍ እስኪያቅተኝ ደረስኩ! ሃያ ስድስት ዓመት ሲሆነኝ ብልሹ ሆኛለሁ፤ አደገኛ ዕጹ እያወፈረኝ ክብደቴ 100 ኪሎ ግራም ሆኖ ነበር፡፡ ከዚያም የአእምሮ መታወክ ውስጥ ገባሁ፤ ከዚያ መውጣትም አስፈሪ ነበር፤ ሲኦል ነበር፡፡ እንዲህ ባለ አስቃቂ ጊዜ አንድ ሰው ስለ ኢየሱስ ነገረኝ፤ ስለ ኢየሱስ የሚነገረኝ ትክክል እንደሆነ ውስጤ ይነግረኝ ነበር፤ ያለማቋረጥም ኢየሱስ ሕያው እንደሆነና እንደሚወደኝ ይነግሩኝ ነበር፡፡ ቃሎቻቸው እንደ ጦር ልቤን ይወጉት ስለነበር የሚሉኝን ማመን ጀመርኩ፡፡ ሁሉንም ነገር ማለትም ባለኝ ነገር ሁሉ ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ ራሴን ክፍት አደረኩኝ፤ ኃጢአት የተሞላ ሕይወቴን በደለኛ መሆኔንና እስራቴን አስተዋልኩት፤ ኢየሱስንም ይቅርታ ጠየኩኝ፤ ውሳኔዬ ጥብቅ ነበር፤ ሕይወቴ በእርግጥ ትርጉም እንዲኖረው ካስፈለገ ኢየሱስ ሙሉ በሙሉ ሊረከበው ይገባል፡፡ በሚገርም ሁኔታም ሕይወቴን ተቆጣጠረው፤ ከአልኮልና ከሃሺሽ እስራት አላቀቀኝ፤ ወዲያውኑ በቅጽበት ሁሉም በደሌ ተወገደ፤ ሸክሜ ቀሎኝ ሕይወቴን በደስታ አጥለቀለቀው፤ የእግዚአብሔር የፍቅሩ ኃይል ፈጽሞ አዲስ ሰው አደረገኝ፡፡

እናም አሁን? አሁን ደስታ ባለው ትዳር ውስጥ ነኝ፤ ሦስት ልጆችም አሉን፤ ኢየሱስ የቤተሰባችንን ሕይወት ስለሚመራው ነገን በድፍረት እመለከተዋለሁ፡፡”

ማይክ

# በእጅጉ ግልጥ የሆኑ ቃላት!

## ደምቀው የሚበሩ እውነቶች

ከሁሉም ዓይነት የማኅበረሰብ ክፍል ያሉ ቁጥር የለሽ ህዝቦች እነዚህን እውነቶች በሕይወታቸው ተለማምደዋቸዋል፤ ይቻላል ብለው አስበውት በማያውቁት መልኩ ሕይወታቸው በላሰቡት ሁኔታ ተለውጧል፤ አስቀድሞ በተስፋ መቁረጥ በጥቃትና ለነገው በመስጋት ይታወክ የነበረው ልባቸው በድፍረት በአስደሳች የደኅንነት እርግጠኛነትና በኑሮ ሐሴት ተሞልቷል፤ ስለ ኢየሱስ እውነተኛነት የሌላቸውና የተጣመሙ ስሜቶቻችሁን እርሷቸው፡፡

ኢየሱስ አለ “እኔ ሕይወት ነኝ” ዮሐ 14፡6
በኢየሱስ የሚያምን ሕይወቱ ዓላማ አለው

ኢየሱስ አለ “እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ” ዮሐ 8፡12
በኢየሱስ የሚያምን ያለረዳት በጨለማ አይንከራተትም

ኢየሱስ አለ “እኔ የሕይወት እንጀራ ነኝ” ዮሐ 6፡35
በኢየሱስ የሚያምን የሕይወት ሙላት አያጣም

ኢየሱስ አለ “እኔ እውነት ነኝ” ዮሐ 14፡6
በኢየሱስ የሚያምን የማይናወጥ መሠረት አለው

ኢየሱስ አለ “እኔ መንገድ ነኝ” ዮሐ 14፡6
በኢየሱስ የሚያምን በቀጥተኛ መንገድ ወደ ግቡ ይራመዳል

ኢየሱስ አለ ”እኔ በር ነኝ” ዮሐ 10፡9
በኢየሱስ የሚያምን ወደ እግዚአብሔር ደርሷል

ኢየሱስ አለ “መልካም እረኛ እኔ ነኝ” ዮሐ 10፡11
በኢየሱስ የሚያምን ድንቅ የሆነውን የፍቅሩን እንክብካቤ ያገኛል

ኢየሱስ አለ “እኔ ትንሣኤ ነኝ” ዮሐ 11፡25
በኢየሱስ የሚያምን ሞትን መፍራት የለበትም

## ቅዱስ፣ ንጹሕ፣ ኃጢአት የሌለው፣ ፍቅር የተሞላ፣ የሚምር፣ ታማኝ፣ መልካምነትን የተሞላ፣ ሁሉን ቻይ፣ እውነተኛ፣ ... ከሁሉ አብልጠው የሚጠሉህ እንኳ ሳይቀሩ ኢየሱስ ፍጹም፣ ልዩ፣ ድንቅ፣ ክቡር መሆንህን ሊቀበሉ ይገባል!

### ኢየሱስ፡ ልብ ወለድ አፈ ታሪክ አይደለም!
ኖሮ እንደማያውቅ እንደ ልበ ወለድ ጀግና እንደ ዊሊያም ቴል ያለ አይደለም ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛና ሕያው ጌታ ነው፤ ፊት እንደነበረው አሁንም በግል ለሰዎች የሚገኝ ነው፡፡ የሃይማኖት መሥራቾች ሁሉም መሞት ነበረባቸው፤ እርሱ ግን ለዘላለም ህልውና ያለው አምላክ ነው፡፡

### ኢየሱስ፡ አቻ የሌለው ድንቅ ነው!
ፍጹም ሰው እንደ መሆኑ እርሱ ያልኖረው የእኛ ኑሮ የለም፤ ስለሆነም ጥልቅ የሆኑ ችግሮቻችንን መፍታት ይችላል፡፡ በእርሱ ምንም ጉድለት ልታገኙ አትችሉም፡፡

### ኢየሱስ፡ ንጹሕ ፍቅር ነው!
ሕዝቡን የሚወደው የእግዚአብሔር ፍጡራን ስለሆኑ ነው፤ ልዩነትን ሳያደርግ ማንንም ሳይንቅ ያፈቅራል፡፡ በማንነታችን እንዲሁ እንዳለን በሙሉ ልብ በፍጹም ፍቅር ይወደናል፡፡ ዮሐ.15፡9-13

### ኢየሱስ፡ ትዕግስትን የተላበሰ ነው!
በማዳመጥና በመከራ ታጋሽ ነው እርሱ ጥልቅ ለሆነውና በብርቱ ለሚቸግረን ጉዳይ ምላሽ ለመስጠት ጊዜውን መስጠት ደስ የሚያሰኘው ነው ዮሐ4፡1-26

### ኢየሱስ፡ እርሱ በፍቅር የሆነ ትኩረት ይሰጣል
እርሱ ለሰው ውድቀት ግድየለሽ አይደለም፤ ክብሩን እየገለጠ የሰበርነውን የጠገነልን ስንት ጊዜ ነው? ኢየሱስ ለሰዎች እንደምን ፍቅርንና ደግነትን ያሳይ እንደነበረ የተመለከቱ ደቀመዛሙርቱ ይደነቁ ነበር፤ ዮሐ.2፡1-2

### አየሱስ፡ ቅድስና ነው!
የሰማያዊ አባቱን የእግዚአብሔርን ክብር በሚመለከት ነገር ሁሉ ኢየሱስ ቀጥተኛ ነበር የእግዚአብሔርን ቤት መሸጫና መለወጫ ለማድረግ የፈለጉትን በብርቱ ተቃወማቸው ቅድስናው አስደናቂ ከመሆኑ የተነሳ ሰዎች የሚቀርቡት በፍርሃት ነበር ዮሐ2፡1-2

ኢየሱስ፡ ሰውን የሚያስብ ነው
አሳቢነቱ በመስቀል ላይ በነበረበት ቢዜ ተገልጧል አሰቃቂ ህመም በሚሰማው ጊዜ እንኳ ልቡ ወደሚወዳት እናቱ ሄደ፤ የሚንከባከባት መኖሩን በጥንቃቄ አረጋገጠ፡፡ የሐ19፡25-27

# ኢየሱስ እንዳንተ ማንም የለም!

### ኢየሱስ፡ ደግነት ነው

ሰዎች ኢየሱስን ተከተሉት፤ በሄደበት ሁሉ ሕዝብ ይከበው ነበር፤ በጥልቅ ጉጉትም ትምህርቱን ይሰሙ ነበር፤ በሺ የሚቆጠሩትን እንጀራና አሳ ይመግብ ነበር፤ እየራበው ወደ ቤቱ የሄደ አንድም አልነበረም፡፡ ዮሐ6፥1-5

### ኢየሱስ፡ ርኅራኄ ነው

ኢየሱስ በኃጢአት ወደተያዙ ወይም በዕዳ ወደተዘፈቁ ሰዎች ጣቱን አይቀስርም፤ ለአታላዮች ለአጭበርባሪዎች ለአመንዝራዎችና ለተንኮለኞች ይራራላቸው ነበር፡፡ ልባቸውን ያውቅ ነበር፤ ወደ ኅሊናቸው ውስጥ በጥልቀት ይመለከት ነበር፤ አንዳንዴም በእንባ ጭምር ያዝንላቸው ነበር፡፡ ችግራቸውንና ሕይወታቸውን በሰንሰለት ያሰረውን ነገር ሁሉ ያውቃል፤ ነጻም ያወጣቸዋል፡፡ ሉቃ.19፥1-10

### ኢየሱስ፡ ለሰው የሚሳሳ ነው

ሰዎች በእጅጉ ምስጢራችን ነው ብለው የሚያምኑትንም ሆነ ጥልቅ ችግራቸውን ለእርሱ ማካፈልን አይፈሩም ነበር፤ ከእርሱ ጋር መሆን መልካም ነበር፡፡ የሰው ነገር የሚያሳሳው በመሆኑ ለሰዎች ችግር የሚሰጠው ምላሽ ከሌሎች የተለየ ነበር፤ ምላሹም ፍቅርን የተሞላና ለሰው የሚሳሳ ነበር፤ ሕጻናት እንኳ ሳይቀሩ ወደ እርሱ መቅረብን ይፈልጉ ነበር፡፡ ሉቃ.8፥40-48

### ኢየሱስ መለኮታዊ ምህረት

ኢየሱስ በሄደበት ሁሉ ሕሙማንን ይፈውስ በመከራቸውም ይረዳቸው ነበር ለሚያስፈልጋቸው ሁሉ ምሕረትን ይሰጥ ነበር፤ መልሶ መላልሶ ሰዎችን ረዳት የለሽ ሆነው ያያቸው ነበርና ፍርሃትን ለተሞላው ልባቸው ምሕረትን ያደርግ ነበር፡፡ ያለ እረኛ እንደተበተኑ በጎች ሆነው ያለ አንዳች ግብ የሚንከራተቱትን ሁሉ ይቀበል ነበር፡፡ ማቴ.9፥36

### ኢየሱስ፡ በጎነት ነበር

አልፎ አልፎ ሙሉ በሙሉ የተጨቆኑ ሰዎች ያጋጥሙት ነበር፤ እርዳታን መልካም የወዳጅ ምክር ፈልገው ወይም ችግራቸውን እንዲረዳላቸው ሲሉ የተከፉበትን ያካፍሉታል፤ ቃሉ ለተጠማችው ነፍሳቸው እንደ ጥም ቆራጭ ውሃ ነበር፡፡ የበዛ በጎነትን ያሳይ ስለነበር በሕዝብ ዘንድ የተናቁት እንኳ ሳይቀሩ ወደ እርሱ ለመቅረብ ድፍረት ነበራቸው፡፡ ማር.1፥40-45

### ኢየሱስ፡ ይቅርታ ነው

በሰው ልብ ያለውን ያውቅ ነበር፤ ለእርሱ ሰው የሚያስበው ነገር እንደተከፈተ መጽሐፍ ነው፡፡ ሰዎችን ከነስህተታቸው ወይም ከነድካማቸው ትቶአቸው አያውቅም፤ ኃጢአታቸውን ግን ያወግዛል፤ ኃጢአቱን ለእርሱ የተናዘዘውን ማናቸውንም ሰው ይቅር ብሎ ልቡን በጥልቅ ሰላም ይሞላል፡፡
ሉቃ.5፥17-26

“ኢየሱስ ሁሌም እኔ ላስበው ከምችለው በላይ ሰጥቶኛል”

“ሟች የሆንንና ከጥላቻ በቀር ሌላ ማሳየት ያልቻልነውን እኛን ወደድህ፤ አንዳችን ሌላውን አሳልፈን ለገዳይ በምንሰጣጥበት አንተ ምሕረት ታደርጋለህ፤ እኛ ድካምንና ውድቀትን በምናይበት አንተ ማበረታታትን ትሰጣለህ፤ ጥላቻን በምናሳይበት አንተ ሰላምን ትሰጣለህ፤ እኛ እኔነትንና ራስ ወዳድነታችንን ስናመልክ አንተ ሕይወትህን ስለእኛ በሞት ሰጠህ”

## ተስፋቢስነት

በኃጢአቶቻችን ተስፋቢስና ለዘላለም ከእግዚአብሔር ፊት የተለየን ያለደኅንነት ወደፍርድ የምንጓዝ ነን የእግዚአብሔር ፍቅር እጅግ በጣም ታላቅ በመሆኑ ለዘላለም እንድንጠፋ አልፈለገም! ልጁንም ኢየሱስን ስጦታ አድርጎ እንዲሰጠን ልቡ በጽኑ ፈለገ፡፡

## ያልዳነ

ምንም ያህል መልካም ቢሆኑ ሥራዎቻችንና ጥረቶቻችን ሊያድኑን አይችሉም ኢየሱስ እንዲመጣ ያስፈለገውም ለዚሁ ነው! የቅዱሱና የጻድቁ አምላካችን ጥያቄ ምላሽ ያገኝ ዘንድ ኃጢአት የሌለበት እርሱ እኛ የምንስት ከመሆናችንና ከኃጢአተኛነታችን የተነሳ ልንቀበለው የሚገባንን መቀበል ነበረበት፤ ለጠፋውና ተስፋቢስ ለሆነው የሰው ዘር ሁሉ ኢየሱስ በቸኛው መዳኛ የሆነውም ከዚህ የተነሳ ነው፡፡ የእግዚአብሔርም ፍጹምና ወሰንየለሽ ፍቅር ተገለጠ!

## ኢየሱስ -

“መዳን በሌላ በማንም የለም እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና” ሐዋ.ሥ 4:12

# ኢየሱስ ክርስቶስ - ፍጹም የተለየ ነው



“በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአበሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዱሁ ወድ፟ዷል”

ዮሐ3፡16

በየተራሮች ላይ የሚታዩት መስቀሎች ስለ ኢየሱስ ድል ይናገራሉ

# ኢየሱስ በመስቀል ላይ

## የእግዚአብሔር ፍቅር የመጨረሻው መገለጫ



### ሉቃስ ምዕራፍ 22 እና 23

ኢየሱስ በመስቀል ላይ የዋለው በራሱ ችግር ምክንያት አይደለም፤ የእግዚአብሔር ድንቅ የደኅንነት እቅድ ነው፤ የከበረ ድል እንጂ የውርደት ሽንፈትም አይደለም፡፡

ኢየሱስ ወደእኛ የመጣው ከአስፈሪው የሲኦል ኩነኔ የሚያድነን አዳኝ ሆኖ ነው

ስለበደላችንና ስለኃጢአታችን በእግዚኣብሔር እንዳይፈረድብን በመስቀል ላይ በሞተው ሞቱ የሚያስፈልገውን ከፈለ

ኢየሱስ ኃጢአታችንን በራሱ በመውሰዱ የእግዚአብሔር ቁጣ በላዩ ወደቀበት እኛ ሁላችን ያለመለየት የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ተላልፈናል

የኢየሱስ በመስቀል ላይ የምትክ መሥዋዕት መሆን ለእኛ ከእግዚአብሔር ዘንድ ሰላምን አስገኘልን፤

እናም የፈሰሰው የኢየሱስ ደም በእውነት ከሁሉም ኃጢአቱና በደሉ ንስሐ የሚገባውን እያንዳንዱን ሰው ያነጻዋል፤

“ተፈጸመ” የሚለው እስከዛሬ ድረስ ከነበረው ሁሉ የከበረ የድል ጩኸት ነው፤

**ተፈጸመ!**

ዮሐንስ 19፡30

# ኢየሱስ ተነሥቷል!

## በኃጢአት፣ በሞትና በዲያብሎስ ላይ ባለድል ሆኗል


ከዋሻ ተፈልፍሎ ወደተሠራ መቃብር የሚያስገባ ደረጃ

### ሉቃስ ምዕራፍ 24

ኢየሱስ በመቃብር ውስጥ አልቀረም፤ በሦስተኛው ቀን ተነሳ፤ ዛሬም ሕያው ነው፡፡ እርሱም ሕያው በመሆኑ በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምኑ የዘላለም ሕይወትን ይቀበላሉ፡፡ በጌታ ኢየሱስ ላይ በግላችን በሚኖረን እምነት ከትንሣኤው ድል እንሳተፋለን በትንሣኤው ኃይል በኢየሱስ ስም በኃጢአት በሞትና በዲያብሎስ ላይ አስተማማኝ ድል አለ፡፡ ሌሎችስ የሃይማኖት መሪዎች በርካቶችን በተጽዕኖአቸው አላስከተሉምን? ዛሬ ወዴት አሉ? እንደማንኛውም የሰው ዘር በሙሉ ሞቱ፤ የመጨረሻውን እስትንፋስ መተንፈስ የነበረባቸው ሙታን ነበሩ፤ ኢየሱስ ግን ይኖራል፡፡

ስለራሱም እንዲህ አለ
“አትፍራ ፊተኛውና መጨረሻው ሕያውም እኔ ነኝ የሞትና የሲኦልም መክፈቻ አለኝ፤»
ራእ.1፡17-18

# ሁለት መንገዶች፣ ሁለት መድረሻዎች፣



## ዘላለማዊ ሕይወት

### ሕይወትን እንምረጥ! የሚያድኑትን የኢየሱስን እጆች እንያዝ፣ ብቸኛ የሆነውን ትክክለኛ ውሳኔ እናድርግ

1. በእግዚአብሔር ፊት መሆናችንንና ከዚህም የተነሳ ቁጣና ፍርድ የተገባን መሆናችንን ልብ እንበል፡፡

2. ኃጢአታችንን በጸሎት በመናዘዝ እርሱን ይቅርታ እንጠይቀው

3. ለእኛ ያለውን ይቅርታውንና ስጦታውን በእምነት እንቀበል፤ የፈሰሰው የኢየሱስ ደም ከማናቸውም ኃጢአት ያነጻናል፡፡

4. በእግዚአብሔር ቃል እንመን እግዚአብሔር በቃሉ የገባውን ተስፋ ምን ጊዜም ይጠብቃል፤ እርሱ ራሱ እውነት ነው፤ ሊዋሽም አይችልም፡፡

# ምርጫው የእኛ ነው!



# ዘላለማዊ ሞት

“ራሱን ለኢየሱስ
አሳልፎ የሚሰጥ
ሰው የሚያጣው ነገር
የለውም፤ ሁሉንም ግን
ያገኛል”

ኢየሱስም አለ “በጠበበው ደጅ ግቡ፤ ወደ ጥፋት የሚወስደው ደጅ ሰፊ፥ መንገዱም ትልቅ ነውና፥ ወደ እርሱም የሚገቡ ብዙዎች ናቸው፤ ወደ ሕይወት የሚወስደው ደጅ የጠበበ፥ መንገዱም የቀጠነ ነውና፥ የሚያገኙትም ጥቂቶች ናቸው።”

*ማቴ.7፡13-14*



# ጸሎት

## በጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር እንነጋገር፤ ስልክ የመደወል ያህል ነውና፡፡

በቀላል ጸሎት ጌታ ኢየሱስን የግል አዳኛህ አድርገህ ልትቀበለው ትችላለህ፤ በጸሎትህ የምትናገራቸውን ቃላት ክብደት ሰጥቶ ይቀበላቸዋል፤ እርሱን ስታናግረው ይሰማሃል፡፡ ሳትረበሽ እርሱን የምታናግርበት ቦታ ፈልግ፤ ወደ እርሱም ቀጥሎ እንደቀረበው ያለ ጸሎት ልትጸልይ ትችላለህ፡፡


ጸጥ ባለ ስፍራ ሁን

“ጌታ ኢየሱስ የጠፋሁ ኃጢአተኛ መሆኔን ከቃልህ እረዳለሁ፤

እናም እፈልግሃለሁ፤ ኃጢአቴንና በደሌን ለአንተ እናዘዛለሁ፤ እስከዛሬ ድረስ ሕይወቴን በገዛ መንገዴ መርቼዋለሁ፤

ስለ ኃጢአቶቼ በእውነት እጸጸታለሁ፤ እባክህን ይቅር ብለህ አንጻኝ፡፡

እባህክህን ውሸቶቼን፣ ጥላቻዬን፣ ምቀኝነቴን፣ ፍቅር አልባነቴንና ሥነምግባር የጎደላቸው መንገዶቼን (እዚህ ላይ የምናውቃቸውን ኃጢአቶቻችንን ዘርዝረን መናዘዝ እንችላለን) ይቅር በለኝ፣

በመስቀል ላይ ደምህ ለእኔም ፈስሶልኛል፤

“በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው” ዮሐ.1፡9




ከእንግዲህ ወዲያ እባክህን ሕይወቴን በማናቸውም ረገድ ተቆጣጠረው፤ እንድሆን ወደምትፈልገው ለውጠኝ፤

አሁን ልቤን ለአንተ ክፍት አድርጌአለሁ፤ አንተን የተቀበለ ሁሉ የእግዚአብሔር ልጅ መሆን እንደሚችል ቃልህ ይናገራል (ዮሐ.1፡12)፤ መጥተህ በሕይወቴ ቀዳሚውን ስፍራ ውሰድ፤ የእግዚአብሔርም ልጅ አድርገኝ፤ አንተ የተስፋ ቃልህን እንደምትጠብቅ ስለማውቅ የራስህ አድርገህ እንደተቀበልከኝ እገነዘባለሁ፤

እባክህ አሁን ከማላስታውሳቸው ኃጢአቶች እኔን ማንጻት ቀጥልበት፤ ከማናቸውም ክፉ የአምልኮተ ባዕድ፣ ጥንቆላ ወይም ሌላ የስህተት አምልኮ እስራት ፍታኝ አንጻኝም፡፡

“ጌታ ኢየሱስ ሆይ የሕይወቴ ጌታ ሆነህ ሕይወቴን ተረከብ፤ ላገለግልህና ወደምትመራኝ ልከተልህ እፈልጋለሁ፤ አሜን፡፡”


ስለ ሕይወትህ አስብ

# ቀጥሎስ?

1. ስለ ደኅንነታችን በየቀኑ ጌታን እናመስግን፤ ስለ ይቅርታውም እናመስግነው፤ ስለ ዘላለም ሕይወት እናመስግነው፤ አሁን የእግዚአብሔር ልጅ በመሆናችን እናመስግነው፤ ይህንን በቃሉ ተናግሯል
ቆላ.1፡1

2. አሁን ሕይወታችን የጌታ የኢየሱስ እንደሆነች ለሌሎች እንንገር፤ ዘላለማዊ ደኅንነትን እንዴት ሊያገኙ እንደሚችሉ ለሌሎች እናስረዳ
1ተሰ.1፡8-10

3. ደስ ይበለን ለዚህም የሚበቃ ብዙ ምክንያት አለንና፤ ክቡር የሆነ ዘላለማዊነት ያለው የወደፊት ሕይወት ይጠብቀናል
1ቆሮ.2፡9

4. ከሌሎች አማኞች ጋር ኅብረትን ማድረግ ጠቃሚ ነው፤ እናም መጽሐፍ ቅዱስን ከምታምን ቤተክርስቲያን ጋር ወይም በቤታቸው መጽሐፍ ቅዱስን ከሚያጠኑት ጋር አንድነትን እንፍጠር
የሐ.ሥ.2፡42

እምነታችንን እየገለጥን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንጠመቅ፤ እግዚአብሔር ይህንን ይጠብቅብናልና መጽሐፍ ቅዱስም ይህንን እንዲህ ሲል ያስረዳል “ቃሉን የተቀበሉ ተጠመቁ”
የሐ.ሥ.2፡41



## እምነት



5. መጽሐፍ ቅዱስን በየቀኑ እናንብብ፤ ያም የእምነትን ድፍረት ትኩስ የሆነ ጥንካሬንና የውስጥ እርጋታን ይሰጠናል፤ እንደዚሁም ክቡር ወደሆነው ግባችን የሚወስደንን ትክክለኛ መንገድን ያሳየናል
ማቴ.4፡4፤ የሐ.ሥ.17፡11

6. በእግዚአብሐር ቃል እንኑር፤ እንደምንወደውና ቃሉን እንደምንፈራ ለእግዚእሔር እናሳይ፤ ለሌሎች ምሳሌ እንሁን፤ እግዚአብሔርን መታዘዝ ተገቢነት አለው፤ ስለዚያም እግዚአብሔር ይባርከናል
ሮሜ 12፡1-2

"በሕይወት የሚገጥሙ ችግሮች በሙሉ በአንድ ላይ የመጡ በሚመስሉበት ጊዜ እንኳ ሁሉንም ነገር ለበጎ ያደርገዋል"

# የሚያድግ ነገር ነው

# ኢየሱስ ተመልሶ ይመጣል!






እርሱም እንዲህ ሲል ቃል ገብቷልና፤

“እነሆም በቶሎ እመጣለሁ” ራእ.22፡7

የመምጫውም ቀን ቅርብ ነው፤ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ የኢየሱስ ትንቢቶች እንደሚፈጸሙ የዘመኑ ምልክቶች ያረጋግጣሉ። ማቴ.24፡ንና ሉቃስ 21ነ2 እናንብብ፤

## ታሪክ ይገለጣል

ኢየሱስ ክርስቶስ በቅድሚያ የሚመጣው ለተቀበሉት እና የእርሱ ለሆኑት ነው 1ተሰ.4፡13-18

ወደ ሰማይ ቤት፣ ወደ እግዚአብሔር ዘላለማዊ ክብር ሊያስገባን መጥቶ ይወስደናል። በዚያ መከራ የለም፤ ከዚያ ወዲያ ሞትም የለም፤ በዚያ በሽታ አያጠቃንም፤ በሰማይ እንባ አይፈስም፤ ሕመምም ዳግመኛ በዚያ አያስጨንቀንም። ጨለማ ከዚያ ወዲያ አያስፈራንም። ያም ዘላለማዊ ቤታችን ነው፤ የተዋጁ የእግዚአብሔር ልጆች ሁሉ ዘላለማዊ ቤት ነው። ራእይ 21

ገጽ 28-31 ተመልከት

# - ይህም አስደሳች እውነታ ነው



“ዓይን ያላየችው ጆሮም ያልሰማው በሰውም ልብ ያልታሰበው እግዚአብሔር ለሚወዱት ያዘጋጀው” ነቆሮ.2:9

ከዚያም ካዳናቸው ከሕዝቡ ጋር ተመልሶ በክፉዎች ላይ ሊፈርድ አለው፤ በሕያዋንና በሙታን ላይ ይፈረዳል፡፡ ሮሜ 2፡8 አንብቡ

እያንዳንዱ ኃጢአተኛ ያለ አንዳች ልዩነት እየተንቀጠቀጠ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ፊት ይሰግዳል፤ ምላስ ሁሉ እግዚአብሔር በፍርዱ ሁሉ ትክክል እንደሆነ እውቅና ይሰጣል፤ አስቀድሞ የተዘበተበት ኢየሱስ ለእግዚአብሔር አብ ክብር በሁሉ ላይ በእርግጥ ጌታ እንደሆነ ይመሰክራል፤ አስቀድመው ያፌዙና የሳቁ ዳግመኛ አይስቁም፤ ግድየለሾችና ለኢየሱስ ጀርባቸውን የሰጡ በፍርሃት ግራ ይጋባሉ፤ ለሠሩት ሥራቸውም ብድራቱን ይቀበላሉ፤ ያም የዘላለም ኩነኔ ነው!

> “ከሞት አፋፍ ላይ ባለና በኢየሱስ ባልዳነ ሰው መኻታ አጠገብ እንደመቆም ያለ የከፋ ነገር የለም”

# የምንቆምበትን እናውቃለንን?



የምንቆምበትን እናውቃለንን? በዚህ ምድር ላይ ያለን ጊዜ የተወሰነ ነው፤ ሞት ለሁላችንም አይቀርልንም፤ ዘላለማዊ ግባችን ምንድነው? ጉዞአችን የሚወስደን ወዴት ነው? ከኢየሱስ ጋር በክብር በሚኖርበት ወይስ ወደ ዘላለም ኩነኔ? ምርጫው የግላችን ነው፡፡

ለማንኛውም ይህች አጭር ሕይወት ምንድን ናት? የቅጽበት እስትንፋስ አይደለችምን? ምናልባት ሙያ ይኖረኝ ይሆናል፤ በሕይወት የምንፈልገውን ሁሉ ያገኘንና የተሳካልን እንሆን ይሆናል፤ ያለ ኢየሱስ ግን ሁሉ ጠፊ ነው፤ ያለ እርሱ ዘላለማዊ ደኅንነት የለም፡፡

እናም አሁን ጊዜ እያለን ትክክለኛ ውሳኔ እንወስን፤ ኢየሱስ እንዲህ እያለ ይጣራል፤ “እነሆ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ፤ ማንም ድምፄን ቢሰማ ደጁንም ቢከፍትልኝ ወደ እርሱ እገባለሁ”

# ውሳኔዬ

ኢየሱስን የግል አዳኜና ጌታዬ አድርጌ ለመቀበል ወስኛለሁ

ስም:

ቀን:

ለተቀበሉት ሁሉ ግን በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው” (ዮሐ.1፡12)

እባክዎ የሚከተለውን ዌብሳይታችንን ይጎብኙ

# www.gbv-dillenburg.de

## The Good Seed, የዕለታዊ ንባብ ካላንደር

የዚህ ካላንደር እያንዳንዱ ገጽ አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ እና ከጥቅሱ ጋር አብሮ የሚሄድ ጽሑፍ ይይዛል፤ አንዳንዶቹ የወንጌል መልእክታት ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ አንባብያንን ለማጠንከርና ለማበርታት የታቀዱ ናቸው።

ይህን ካላንደር በwww.gbv-online.org በቀጥታ ማንበብ ይቻላል፤ እንዲሁም ነጻ የሆነውን “The Good Seed” የሚለውን መተግበሪያችንን አውርዶ መጠቀም ይቻላል።

GET IT ON Google Play

Download on the App Store




# www.gbv-online.org




- ✓ የተለያዩ ቋንቋዎች
- ✓ ለመጠቀም ነጻ የሆኑ
- ✓ መጻሕፍት

# ኢየሱስ

ከኢየሱስ ክርስቶስ ሌላ ይበልጥ የመነጋገሪያ ርእስ የሆነ ሌላ አካል የለም፤ አንዳንዶች ይወዱታል፤ ሌሎች ይጠሉታል፤ ሆኖም አብዛኞቹ ስለ “ኢየሱስ” የሚነገረው ርእስ ስለማይመቻቸው ይተውታል፡፡

እርሱ ሰዎችን ከማንም በላይ ያውቃል፤ ቃሎቹ እውነት ናቸው፤ እርሱን በተመለከተ እያንዳንዱ የት እንደቆመ በግልጽ ያውቃል፤ በእርሱ እንደሆነው ብዙ አለመስማማትን ያመጣ ማንም የለም፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ በመጣበት በየትም ስፍራ በተለየ ሁኔታ ወደ እርሱ የሚጠጉት ድሆች፣ በሽተኞች እና በማኅበረሰቡ የተገፉ እንደሆኑ ይስተዋላል፡፡

ኢየሱስ - የእርሱ ወገን ለሆኑት ጆሮዎች ስሙ እንደ ጥዑም ዜማ ነው፤ ለተቃዋሚዎቹ ግን የሚያውካቸው ነው፤ ሚሊዮኖች ሕያው መሆኑን እየተናገሩ ሳለ፣ እነርሱ እንደሞተ ብቻ ስለሚያስቡት ስለ እርሱ መጻሕፍትን ለመጻፍ ጣታቸውን የሚያነሱት ለምንድን ነው?

ሆኖም በእያንዳንዱ ነገር እርሱ የተናገረውንና ያደረገውን ነገር ብትመለከቱ ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛው ብቸኛ ተስፋችን እንደሆነ ታውቃላችሁ፡፡





ISBN: 978-3-96162-649-6

GBV 115 4560 Jesus Our Only Real Hope (Amharic)